38

# የተሻሻለው የኢትዮጵያ የወንጀል ረቂቅ ሕግ አጭር ማብራሪያ (መግለጫ)

## መግቢያ

ሕጎች በህብረተሰቡ ውስጥያሉ ግንኙነቶችን የስመረ ለማድረግ እንደአስፈላጊነቱ በየወቅቱ የሚሻሻሉ መሆኑ ይታወቃል። በአንድ በኩል በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ግንኙነቶች በውስጣዊ ወይም በውጭአዊ ሁኔታዎች ተገፋፍተው ለውጥን ሲሹና ግንኙነቱን የሚገዙት ሕጎች ደግሞ የገቺነት ጠባይ ሲያሳዩ፣ ለውጡን ተከትሎ ሕጉን ማሻሻል ተገቢ ይሆናል። በሌላ በኩል የለውጥ ሁኔታዎች ባልበሰሉበትና ባልተመቻቹበት ነገር ግን የለውጥ አራማጆች ራዕይ አድማስን በመከተልም ለውጡን ለማፋጠን ሕጎች ሊሻሻሉ ይችላሉ። በአጠቃላይ ሕጎች በባህርያቸው ወቅትን እየጠበቁ እንደሚሻሻሉ ከታሪክ መረዳት ይቻላል።

በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የወጣው በቁ.1/1949 ነጋሪት ጋዜጣ ሐምሌ 16 ቀን 1949 ዓ.ም. ሲሆን በሥራ ላይ የዋለው ግን ከሚያዝያ 27 ቀን 1950ዓ.ም. ጀምሮ ነው።

በወቅቱ ሕጉ አገሪቱ ከነበረችበት የዕድገት ደረጃ ጋር ሲታይ በእጅጉ ዘመናዊ ይዘት የነበረው በአንጻሩም የአገሪቱን ባሕል የተላበሰም እንደሆነ ስቴቨን ሎዊንሽታይን የተባሉ የሕግ ምሁር በኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ቮልዩም 2 ቁጥር 2 ውስጥ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ እቅድ በተባለው ጽሁፋቸው "... ይኸ ሕግ ከጥንት የነበረውን የኢትዮጵያን የሕግ ልማድ በቅርብ ጊዜ ከወጡት ከአውሮፓ ክፍለ ዓለም አዳዲስ ሕጎች አብዛኛውን አዋህዶ የያዘና የተራቀቀ ዘመናዊ ሕግ ነው" በማለት ገልጸውታል።

በሥራ ላይ ያለውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ለአራት አስርት ዓመታት ያህል ሕግ አስከባሪዎች እና ፍርድ ቤቶች እንዲሁም ሕግ ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ ህብረተሰቡ ሲገለገሉበት ቆይተዋል።

ከዚህም በኋላ በየጊዜው በሚወጡ ተናጠል ሕጎች የወጡበትን ጉዳይ የተመለከተ የወንጀል ድንጋጌ እየታከለበት አንዳንዴም የወንጀል ድንጋጌው



ethcriminalawnetwork.com

በሥራ ላይ ወደአለው የ1949ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እያጣቀሰ ወይም እየመራ በዚህ መልክ እንደመሻሻል የሚቆጠር ሥራ ተሰርቷል።

በሥራ ላይ ያለው የ1949 ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተናጠል በሚወጡ የወንጀል ሕጎች ሳይሆን ጠቅላላ መጽሐፉን ለማሻሻል በፍትሕ ሚኒስቴር ሥር በሚመራ የአርቃቂ ኮሚቴ ሲሰራ ቆይቶ በ1976 አንድ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ነበር።

ሆኖም ይህ ጥረት ከረቂቅነት ባለማለፉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ሲሰራበት ቆይቷል። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ የህጉን መሻሻል የሚጠይቁ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። ይኸውም፤

1. ዛሬ በምንገኝበት የሶሻል፣ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶች ያስከተሏቸው ክስተቶች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን ማሻሻል የጠየቁ በመሆናቸውና ይልቁንም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ውስጥ የተካተቱ ሰብአዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነጻነቶች ጋር መጣጣም የሚገባቸው ጉዳዮች በመኖራቸው፤

2. በዓለም አቀፍም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ የተለየ ትኩረትን የሚሹ እንደሙስና፣ የአውሮፕላን ጠለፋ፣ የዕጽ ዝውውር፣ ሽብርተኝነት ያሉ ወንጀሎች በሥራ ላይ ባለው ሕግ በበቂ ሁኔታ ባለመሸፈናቸው እነዚህን ማካተት በማስፈለጉ፤

3. ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ እንድታሟላ የተጣለባትን አንዳንድ ግዴታዎች በተቻለ መጠን በሕጉ ውስጥ ማጠቃለል አግባብ በመሆኑ፤

4. በህግ አስፈጻሚዎችና በፍርድ ቤቶች በኩል በአፈጻጸም ረገድ በሥራ ላይ ያለው ሕግ ታይተውበታል የሚሏቸውን ችግሮች ማስተካከል በማስፈለጉ፤

5. በሌሎችም አገሮች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎችን ከዘመኑ ጋር ለማራመድ የማሻሻል ተግባር በቀጣይነት የሚከናወን እንደ መሆኑ ከዚሁ አንጻር በሥራ ላይ ያለውን ሕግ ማሻሻል ጠቃሚ በመሆኑ፤

በፍትሕ ሚኒስቴር የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን የሚያሻሽል ኮሚቴ ተዋቅሮ ይህንን ረቂቅ አዘጋጅቷል።


ethcriminalawnetwork.com

ለዓውደ ጥናቱ የውይይት መንደርደሪያ ይሆን ዘንድ በተሻሻለው የወንጀለኛ መቅጫ ረቂቅ ህግ ላይ የተደረጉት ዋና ዋና ማሻሻያዎች በማብራሪያ መልክ ቀርበዋል።

## I. ጠቅላላ ለውጦች

በተሻሻለው ረቂቅ ሕግ ውስጥ የሚከተሉት ጠቅላላ ለውጦች ተካትተዋል፤

1. በሥራ ላይ ያለው ሕግ ርዕስ "የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ" ይል ነበር። ነገር ግን ይህ ስያሜ ቅጣትንና የቅጣት አወሳሰንን ብቻ የሚያመለክት ይመስላል። የሕጉ ይዘት ሲታይ ግን ወንጀልን የሚዘረዝር እና ለየወንጀሉ የሚጣሉ ቅጣቶችንና የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን የያዘ በመሆኑና ይህንን የሚያንፀባርቀው ስያሜ ደግሞ "የወንጀል ሕግ" የሚለው በመሆኑ በዚሁ መሠረት የረቂቁ ስያሜ "የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ" እንዲባል ሆኗል። ይህ አገላለጽ በሕገ መንግሥት አንቀጽ 23 ላይ ከሰፈረው አገላለጽ ጋር የሚስማማ ነው።

2. በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ "Title" ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "አንቀጽ" በሚል የተሰጠው ትርጓሜ አሁን ከተመለከተው ቃል ጋር እንዲጣጣም "ርዕስ" ተብሏል።

3. በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ "Article" ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "ቁጥር" ተብሎ የተሰጠው ትርጓሜም አሁን ከተለመደው አጠቃቀም ጋር እንዲጣጣም "አንቀጽ" ተብሏል።

4. በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ "Principle" ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "መሠረቱ" ተብሎ የተሰጠው ትርጉምም አሁን ከተለመደው አጠቃቀም ጋር የተጣጣመ እንዲሆን "መርህ" ተብሏል።

5. የሕጉን አደረጃጀትና የአንቀጽ ቅደም ተከተል ላለማፋለስ ግን ጥንቃቄ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት የሕጉ አጠቃላይ አከፋፈል እንዲጠበቅ ሆኖ አንቀጾችን በሚመለከት ግን የሚሠረዘው "ተሰርዟል" ተብሎ የተገለጸ ሲሆን ያልተሰረዘው ግን የቀድሞውን የአንቀጽ ቁጥር ሳይለውጥ እንደነበረ እንዲሆን ሆኗል። አዲስ የሚገባ አንቀጽ ሲኖር አንቀጹ ከሚገባበት በፊት የነበረውን አንቀጽ ቁጥር በመጠቀም አዲስ አንቀጽ መሆኑን ለማመልከት ግን ከቁጥሩ ፊት ለፊት "ሀ" ወይም "ለ" የሚል ፊደል ተጨምሮበት ተቀርጿል። ለምሳሌ ከአንቀጽ 252 ቀጥሎ ሌላ አዲስ አንቀጽ ሲገባ አዲሱ



ethcriminalawnetwork.com

አንቀጽ 252 (ሀ) ተብሎ ተሰይሟል። ይህ የተደረገበት ምክንያት በራሱ በሕጉ ውስጥም ሆነ በሌሎች ቅጣትን በሚደነግጉ ልዩ ልዩ አዋጆች የተጣቀሱ የሕጉን አንቀጾች ላለማዘበራረቅ ታስቦ ነው። ነገር ግን በመንግሥት ሥራና በማህበራዊ አገልግሎት ሥራ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (ከአንቀጽ 410 - 437) በሚለው ርዕስ ሥር የአንቀጽ ቅደም ተከተል መፋለስና መደባለቅ እንዲሁም የቦታ ለውጥ ተደርጓል። ይህም የተደረገው ወንጀሉን በተሟላ ሁኔታ በዘመናዊ መልክ መቅረጽ በማስፈለጉ ነው። ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚመጡ አንቀጾች ግን ቀደም ሲል በነበሩበት ሁኔታ ሳይፋለሱ እንዲወጡ ተደርጓል።

## II. <u>በሕጉ ጠቅላላ ክፍል (ከአንቀጽ 1- 247) ላይ የተደረጉ ለውጦች</u>

### 1. <u>በአጠቃላይ</u>

በዚህ ክፍል ውስጥ፤

- አላስፈላጊ አንቀጾች ተሰርዘዋል። የተሰረዙበት ምክንያትና የተሰረዙበት አንቀጾች በየአንቀጹ ላይ በተሰጠ ማብራሪያ ላይ ተገልጿል።

- የቅጣት መነሻውም ሆነ ጣራው (የገንዘብም የእሥራትም) ከፍ ብሏል። ዝርዝሩ በየአንቀጹ ላይ ተገልጿል።

- የቅጣቱን መነሻና ጣሪያ ተከትሎ የይርጋ ጣሪያውም ከፍ ብሏል።

- የተደራረቡ ወንጀሎች በተፈጸሙ ጊዜ የእሥራቱም ሆነ የገንዘብ ቅጣት አወሳሰን መርሁ ተለውጧል። በዚህም መሠረት ለከባድ ወንጀል ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ለሌላው ወንጀል እስከ መጀመሪያው ቅጣት ግማሽ ድረስ ይጨመር የነበረበት (የአግራቬሽን) መርህ ቀርቶ ለየቅጣቱ ዓይነት የተወሰነውን ጣሪያ አስካላለፈ ድረስ ለሁሉም ወንጀሎች የሚወሰኑ ቅጣቶች እንዲደመሩ ሆኗል። /ዝርዝሩ በአንቀጽ 189 እና 191 ላይ ተገልጿል/።

- በሕጉ ልዩ ክፍል ላይ የተጠቀሱ ወንጀሎች በሕግ የሰውነት መብት ባለው አካል በተፈጸመ ጊዜ እና



ethcriminalawnetwork.com

ግንዛቤ በማግኘቱ ድርጊቱን በወንጀል ሕጎች እንደጥፋት መቅረጽ ተለምዷል።

በመሆኑም በረቂቁ ውስጥ ማንኛውም ወንጀል የሕግ ሰውነት ባለው ተቋም ተፈጽሞ ሲገኝ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑ ተደንግጓል። ይህ ድንጋጌም በአንቀጽ 33 ሥር ንዑስ ቁጥር 2 ሆኖ ተረቅቋል። ይህ ሥፍራ የተመረጠበት ምክንያት፣ አንቀጽ 33 የሚያወሳው ለወትሮው በባህሪያቸው የተወሰኑ ወንጀሎችን መፈፀም አይችሉም ተብለው የሚገመቱ ወገኖች በተካፋይነት ከሌላው ጋር እነዚህን ወንጀሎች ፈጽመው ሲገኙ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ነው። በሌላ አነጋገር ድንጋጌው በባህርይ የተወሰነ ወንጀልን አይፈጽምም ተብሎ የሚገምት ወገን በዚሁ ወንጀል ተጠያቂ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል። በአንጻሩ በህግ ሰውነት በተሰጠው አካልም ለወትሮው 'Malainse' የተባሉትን ወንጀሎች ለምሳሌ እንደ ግድያ ያሉትን መፈፀም አይችሉም ሲባል የቆየውን አስተሳሰብ በመናድ ሊፈጽሙ እንደሚችሉ የሚያሳይ ሁኔታ ያንጸባረቀ አዲስ ድንጋጌም በሥራ ላይ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአንቀጽ 33 ላይ ያለውን መርህ የሚጋራ በመሆኑ፣በዚሁ አንቀጽ 33 ሥር ሊደነገግ በቅቷል።

## ከአንቀጽ 41 - 48

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚከተሉት ለውጦች ተደርገዋል።

1. ርዕሱ "ታትመው በሚወጡ ጽሑፎች በሚሠራ ወንጀል ተካፋይ ስለመሆን" ይል ነበረ። ይህ ስያሜ ከሕትመት ውጭ ያሉ የፕሬስ ሥራዎችን የማይሸፍን ስለሆነ ይህንኑ ለማስወገድ "በሕትመት ወይም በሌሎች የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በሚፈፀሙ ወንጀሎች ተካፋይ ስለመሆን" ተብሏል። በዚሁ መሠረት ከአንቀጽ 41 - 48 ባሉት ድንጋጌዎች ላይ ይኸው አነጋገር በወጥነት እንዲያገለግል ተደርጓል።

2. በፕሬስ ሥራዎች በሚፈጸሙ ወንጀሎች ውስጥ ኃላፊ መሆንን በተመለከተ ለሕትመት ሥራዎች ሲሆን በአንቀጽ 43 ላይ ለሌሎች ደግሞ በአንቀጽ 45 ላይ የተለያዩ መርሆች መቀመጡ ቀርቶ ለሁሉም ሁኔታዎች ተመሳሳይ መርህ ለማስቀመጥ አንቀጽ 43 እና 45 ተዋህደው ስለተቀረጹ አንቀጽ 45 ተሰርዟል።

3. በፕሬስ ሥራዎች ወንጀል ሲፈጸም ተፈጸመ የሚባለው በየትኛው ደረጃ ላይ ነው የሚል አከራካሪ ሀሳብ ስለነበረ ይህንን አከራካሪ ሁኔታ ለማስወገድ እና በአሁኑ ጊዜ ያለውን የሴንስርሺፕ መቅረት ለማንጸባረቅ ሲባል በአንቀጽ 41(3) መጨረሻ ላይ "ወንጀሉ ተፈጸመ የሚባለውም በነዚሁ ዘዴዎች



ethcriminalawnetwork.com

ለሕዝብ በተገለጸ ጊዜ ነው" የሚል አረፍተ ነገር እንዲገባ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት ለሕዝብ ከመገለጹ በፊት ያለውን ሁኔታ እንዳይሸፈን ተደርጓል።

4. በኘሬስ ወንጀል ጊዜ የሚስጥር ነፃነትን ለማረጋገጥ ሲባል ኃላፊነት ያለበት ሰው ፀሐፊውን፣ ሰዓሊውን ወይም ሌላውን ለመግለጽ ባልፈለገ ጊዜ የመርማሪዎች ማስገደድ እንዳይኖርበት ታስቦ መገደድ የሚኖረው "ፍርድ ቤት ባዘዘ ጊዜ ነው" የሚል ሀሳብ በአንቀጽ 44(1) ላይ እንዲገባ ተደርጓል። ፍ/ቤቱ የመገደድ ትዕዛዝ ሲሰጥም በሕጉ ውስጥ በሰፈሩት ሁኔታዎች ብቻ ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ተወስዶ የተቀረጸ ነው።

## አንቀጽ 49

በአንቀጽ 49(1) መንደርደሪያ ላይ "ከዚህ በላይ ባለው አንቀጽ በተመለከቱት ምክንያቶች" የሚል ገብቷል። ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት ለማስወገድ እና ከፊል ኃላፊነትን ለማስወገድ የተቀመጡት ምክንያቶች ተመሳሳይ ሆነው ልዩነቱ ግን የጉዳቱ መጠን ብቻ እንደሆነ ለማመልከት ታስቦ የተደረገ ነው።

## አንቀጽ 60

በአንቀጽ 60(1) ላይ ከአንድ ሰው ወይም በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ ወይም የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች በአንድ ሀሳብ በተሰሩ ጊዜ እንዳንድ ወንጀል የሚቆጠሩበት ሁኔታ ብዙ የሚያስቸግር ሆኖ ተገኝቷል። ይህንን ችግር ለማስወገድ ታስቦ በአንድ ሀሳብ መሠራታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ "ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ከሆነ" ብቻ እንደ አንድ ወንጀል እንዲቆጠሩ በአንድ ድንጋጌ የማይሸፈኑ ከሆነ ግን አንደተደራራቢ ወንጀል እንዲቆጠሩ ተደርጎ ተቀርጿል።

## አንቀጽ 77

የዚሁ አንቀጽ ይዘት በአንቀጽ 2 ላይ የተሸፈነ እና አላስፈላጊ ስለሆነ ተሰርዟል። ምክንያቱም በአንቀጽ 2(2)ላይ አስቀድሞ በሕግ ወንጀል ነው ያልተባለ ድርጊት ሲፈጸም እንደማያስቀጣ ተደንግጓል። ስለሆነም አድራጊው ወንጀል የፈጸመ ቢመስለው ሕጉ ወንጀል ነው ካላለ ስለማያስቀጣ በዚሁ መሠረት አንቀጽ 77 ተሰርዟል።


ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 88

ይህ አንቀጽ የገንዘብ ቅጣት አወሳሰን መርህን እና አጠቃላዩን ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የቅጣት ወሰን የሚደነግግ ሲሆን በተሻሻለው ረቂቅ ላይ የሚከተሉት ለውጦች ተደርገዋል።

1. ቀደም ሲል በነበረው ሕግ ላይ የገንዘብ ቅጣት መነሻው አንድ ብር ሆኖ ከፍተኛው 5000 ብር ነበር። ነገር ግን አሁን ያለውን እና ወደፊትም ሊኖር የሚችለውን የብር ዋጋ ከግምት ውስጥ ያላስገባ ስለሆነ በዚሁ መሠረት መነሻው 10 ብር ሆኖ ጣሪያው እስከ 50,000 ብር እንዲደርስ ተደርጓል።

2. በአንቀጽ 33(2) መሠረት ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል በወንጀል ተጠያቂ በሚሆንበት ጊዜ የገንዘብ ቅጣቱ ጣሪያ እስከ 500,000 ብር እንደሚደርስ ተደንግጓል። ነገር ግን ልዩ ሕጉ የገንዘብ ቅጣትን ባልደነገገ ጊዜ እሥራቱ ወደገንዘብ ተለውጦ የሚቀርብበት ሁኔታም በአንቀጽ 88(4) ላይ ተደንግጓል። በዚሁ መሠረት እስከ 5 ዓመት እሥራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ 20,000 ብር ፤ ከ5 - 10 ዓመት እሥራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ 50,000 ብር ፣ ከ10 ዓመት እሥራት በላይ ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ 500,000 ብር ሆኖ ተመልክቷል። ይህ ድንጋጌ ግን በሕጉ ውስጥ በተለየ ሁኔታ ከፍ ብሎ የተደነገገ ቅጣት ካለ ተፈጻሚነቱን አያከላክልም። ምናልባት የእሥራት ወደ ገንዘብ አለዋወጥ መሠረት ምን እንደሆነ አጠያያቂ ይመስላል። ነገር ግን ከአሁን በፊት በሥራ ላይ ባለው ሕግ በአንቀጽ 510 እና 567 ላይ የተደነገጉትን የእሥራት እና የገንዘብ ቅጣቶች በማነፃጸር እና አሁን ያለውን የገንዘብ ዋጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት በአማካኝ የተወሰደ ነው። የተለየ ቀመር የሚገኝለት ከሆነ ሊለወጥ ይችላል።

## አንቀጽ 90

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ በተሰራ ጊዜ ቀደም ሲል የነበረውን 10,000 ብር ወደ 100,000 ብር ከፍ ተደርጓል። ይህም የሆነው ከላይ በአንቀጽ 89 ላይ የተደረገውን ለውጥ በመከተል ነው።

## አንቀጽ 94

በዚህ አንቀጽ ውስጥ አንድ ተቀጪ መቀጮ መክፈል ባልቻለ ጊዜ በእሥራት ተለውጦ ይቀጣል ከሚል በስተቀር የገንዘብ ቅጣቱ ወደ እሥራት የሚለወጥበት ሁኔታ ለፍ/ቤቱ የተተወ ነበር። ነገር ግን



ethcriminalawnetwork.com

ይህን አሠራር መለወጥ በማስፈለጉ መቀጮው ወደ እሥራት በሚለወጥበት ጊዜ የአንድ ቀን እሥራት በብር 10 ሂሳብ ሆኖ በጠቅላላ ግን ከ5 ዓመት መብለጥ እንደሌለበት ተደንግጓል። ይህም ማንኛውንም ዓይነት ገቢ በቀን ለሚያገኝ ሰው የሚያገለግል ነው።

ነገር ግን መቀጮ ወደጉልበት ሥራ በሚቀየርበት ጊዜ ለአንድ ቀን የጉልበት ሥራ የሚታሰበው ዝቅተኛ ግምት በቀን 5 ብር እንዲሆን ተደርጓል። ይህም ተመን ዛሬ ለአንድ የጉልበት ሠራተኛ በቀን የሚታሰበውን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው በቀን ከዚህ በላይ ገቢ የሚያስገኝ ሠራተኛ በዚያው መሠረት ይታሰብለታል።

ከዚህም ሌላ ቀደም ሲል በአንቀጽ 96 ላይ ሰፍሮ የነበረው ድንጋጌ የአንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ (3) ሆኖ ገብቷል። ይህም የተደረገው ፍርድ ቤቱ በየደረጃው የሚወስዳቸው እርምጃዎች በአንድ አንቀጽ ሥር ቢጠቃለል አመቺ ይሆናል ተብሎ ታስቦ ነው። ስለሆነም አንቀጽ 96 ተሰርዟል

## አንቀጽ 96

ይህ አንቀጽ የአንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ (3) ሆኖ ስለገባ ተሰርዟል።

## አንቀጽ 105

ይህ አንቀጽ የቀላል እሥራት ቅጣትን ዝቅተኛና ከፍተኛ ወሰን የሚደነግግ ነው። ቀደም ሲል ባለው ሕግ ውስጥ ዝቅተኛው ቅጣት 10 ቀን ከፍተኛው 3 ዓመት ነበረ። በተሻሻለው ረቂቅ ላይ ግን ዝቅተኛው አንድ ወር ከፍተኛው 5 ዓመት እንዲሆን ተደርጓል። ስለሆነም ከአንድ ወር በታች እሥራት የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ በደንብ መተላለፍ የሚታይ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ ቀደም ሲል የነበረው ከፍተኛ ቅጣት 3 ዓመት መሆኑ ሲታይ አሁን በተለያዩ አዋጆች ከሚጣሉ ቅጣቶች አንፃር ሲታይ አነስተኛ ሆኖ ስለተገኘ ወደ 5 ዓመት ከፍ እንዲል ተደርጓል።

## አንቀጽ 107

ይህ አንቀጽ የጽኑ እሥራትን ዝቅተኛ እና ከፍተኛ ወሰን የሚደነግግ ነው። ቀደም ሲል ከነበረው ሕግ ውስጥ ዝቅተኛው 1 ዓመት ሲሆን ከፍተኛው 25 ዓመት ነበረ። በተሻሻለው ረቂቅ ላይ ግን ከ1-30 ዓመት እንዲሆን ተደርጓል። ይህም የተደረገው በብዙ አገሮች ሕጎች ውስጥ የ30 ዓመት ጣሪያ የተለመደ በመሆኑ ነው።


ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 112

በዚህ አንቀጽ ውስጥ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የተፈረደበት ሰው አመክሮ የሚፈቀድለት 25 ዓመት ሲጨርስ ነበር አንቀጹ መሠረት ያደረገው ቀደም ሲል በነበረው ሕግ በአንቀጽ 107 ላይ የተደነገገውን ከፍተኛ የእሥራት ቅጣት ስለነበረ በዚሁ መሠረት ያሻሻለው ረቂቅ ይህንኑ ተከትሎ ወደ 30 ዓመት ከፍ እንዲል ተደርጓል።

## አንቀጽ 116

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኖ የሚከተለው አዲስ ሀሳብ ገብቷል። "ከሚያስከትለው ከባድ ጥፋት የተነሳ ወይም በጠቅላላው በሚያደርሰው አደጋ መጠን በሕጉ በግልጽ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ወንጀልን ለመሥራት በተደረገ መሰናዳት ወይም ሙከራ የሞት ቅጣት ሊወሰን አይቻልም።" ይህ ድንጋጌ እንዲገባ የተደረገው በአንድ በኩል በአንቀጽ 27 እና 40 ሥር በሠፈሩት መርሆዎች መሠረት ፍጻሜ ላገኙ ወንጀሎች የተደነገጉ ቅጣቶች በተሞከረ ጊዜ የሞት ቅጣት እንዳይወሰን ለመከላከል። በሌላ በኩል ደግሞ መሰናዳቱና ሙከራው ከባድ ወንጀል በሆነ ጊዜ ፍጻሜ ባያገኙም እንዳገኙ ተቆጥረው የሚያስቀጡ በሆነ ጊዜ የሞት ቅጣት መወሰንን እንዳይከላከል ታስቦ የተደረገ ነው።

2. በአንቀጽ 116(2) ላይ ደግሞ "የሞት ቅጣትን በተመለከተ ስለመከላከያ ሠራዊት በልዩ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ. . . "የሚል ገብቷል። ይህ የተደረገው መከላከያ ሠራዊትን በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው የመከላከያ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ በመሆኑ ያንን አፈፃፀም እንዳያውክ ታስቦ ነው በሌላ ሁኔታ ግን የሞት ቅጣትን የሚያጸናው የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር እንደሆነ ተደንግጓል። በዚህ ነጥብ ላይ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች በክልል ፍ/ቤቶች በሚሰጡ የሞት ቅጣቶች ላይ ሥልጣን ይኖራቸዋል ወይስ አይኖራቸውም የሚል ክርክር ተነስቶ ነበረ። ነገር ግን የተመረጠው ሀሳብ ለፌደራሉ ርዕሰ ብሔር ይሰጥ የሚለው ስለሆነ በዚሁ መሠረት ተቀርጿል። ከዚህም ሌላ የሞት ቅጣት የሚጸናበት ሥርዓት በዚህ ሕግ ላይ ይግባ ወይስ አይግባ ? የሚለው ነጥብ አከራክሯል። ከብዙ ውይይት በኋላ ራሱን በቻለ ሌላ ሕግ ሊወሰንና ሥርዓት ሊበጅለት ይገባል የሚለው ሀሳብ ተቀባይነት ስላገኘ በዚሁ መሠረት ሥርዓቱን የሚመለከት ድንጋጌ በሕጉ ላይ አልሰፈረም።



ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 120 (ሀ)

በዚህ አንቀጽ ላይ የሰፈረው የግርፋት ቅጣት በሕገ መንግሥቱ ላይ ከሰፈሩት የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች ጋር በተለይም ከአንቀጽ 16 እና 18(1) ጋር የሚጻረር ስለሆነ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

## አንቀጽ 146

በዚህ አንቀጽ ውስጥ የሥራ ፈቃድ የሚሰጣቸውን የሥራ ዓይነቶች ይዘረዝር ስለነበረና ዝርዝሩ ደግሞ የተሟላ ባለመሆኑ ይህ መሆኑ ቀርቶ ለልዩ ልዩ ተግባር ማከናወኛ የሚሰጥ ፈቃድ በሚል በአጭሩ ተስተካክሏል። ከዚህም በተጨማሪ በአንቀጽ 33(2)ሥር በሰፈረው ሀሳብ መሠረት በሕግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል የሚሰጥ ፈቃድንም እንዲጨምር ሆኖ ተቀርጿል።

## አንቀጽ 172

ይህ አንቀጽ ወጣት አጥፊን በአለንጋ ወይም በአርጩሜ መግረፍን የሚደነግግ ስለነበረ ይህ ደግሞ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 16 እና 18(1)ጋር የሚቃረን ስለሆነ ተሰርዟል።

## አንቀጽ 184

ይህ አንቀጽ ቅጣትን የሚያቃልሉ ምክንያቶች በተገኙ ጊዜ ቅጣት የሚቀልበትን ሁኔታ የሚደነግግ ነው። በአዲሱ ረቂቅ ላይ ያለውን የቅጣት መነሻ እና ጣሪያ መሠረት አድርጎ የማቃለል ሀሳቡም እንዲለወጥ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት:-

- በ'ሀ' ላይ በሞት ቅጣት ምትክ ከ20 ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ ይል የነበረው ከ25 ዓመት እስከ እድሜ ልክ ተብሏል።
- በ'ለ' ላይ በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ምትክ ከ10 - 20 ዓመት ይል የነበረው ከ15 - 25 ዓመት ተብሏል።
- በ'ሐ' ላይ ለውጥ አልተደረገም፣
- በ'መ' ላይ ለውጥ አልተደረገም፣
- በ'ሠ ' ላይ በ10 ቀን ምትክ 30 ቀን ሆኗል፣
- በ'ረ' ላይ ለውጥ አልተደረገም፣



ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 189

ይህ አንቀጽ ወንጀሎች በተደራረቡ ጊዜ የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን የሚያስቀምጥ ነው። በአዲሱ ረቂቅ ሕግ በፊት የነበረውን መርህ በመለወጥ በአዲስ እንዲተካ ተደርጓል። በዚህ መሠረት የተደረጉት ለውጦች የሚከተሉት ናቸው።

1. በአንቀጽ 189(1) (ሀ) ላይ ከብዙ ቅጣቶች መካከል አንዱ በሞት የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ የሞት ቅጣቱ ሌሎችንም ያጠቃልላል የሚል ድንጋጌ ነበረው። ነገር ግን ከብዙ ጥፋቶች መካከል አንዱ ወይም ሁለቱ የእድሜ ልክ እሥራት የሚያስቀጡ በሆነ ጊዜ ምን ይሆናል የሚለውን ጥያቄ የማይመልስ ስለነበረ ይህንን ችግር ለመቅረፍ አንዱ የዕድሜ ልክ እሥራት ሁሉንም እንደሚያጠቃልል ተገልጾ ተደንግጓል።

2. ከአንድ በላይ የሆኑ ነፃነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች ባጋጠሙ ጊዜ በፊት በነበረው ሕግ ላይ አንቀጽ 189(1) (ለ) ላይ ተቀምጦ የነበረው መርህ ለከባዱ ጥፋት የተወሰነውን ቅጣት መሠረት አድርጎ በመያዝ ለሌሎቹ ጥፋቶቹ የዚህኑ ቅጣት እስከ ግማሽ ያህል ድረስ በመጀመሪያው ቅጣት ላይ በመጨመር ይወሰን ነበረ። ይህ መርህ Aggravation በመባል ይታወቃል። በአዲሱ ረቂቅ ላይ ግን ይህ መርህ ተለውጦ ለየመደቡ የተወሰነውን (ለእሥራት ወይም ለገንዘብ) ከፍተኛ ጣሪያ እስካላለፈ ድረስ ሁሉንም ቅጣቶች መደመር እንዲሆን ተደርጓል። ይህ መርህ የመደመር (Cummulation) መርህ በመባል ይታወቃል። ይህ መርህ ለአፈጻጸም የሚያመች እና በብዙ አገሮችም የሚሠራበት በመሆኑ ሊመረጥ ችሏል። በዚህ የቅጣት ስልት መሠረት የሚደመረው የቅጣት ጣሪያ በህጉ ላይ ከተወሰነው በላይ ማለፍ አይችልም። ለምሳሌ የፅኑ እሥራት ጣሪያው 30 ዓመት መሆኑ በዚህ ረቂቅ አንቀጽ 107 ላይ ተደንግጓል አንድ ተከሳሽ፣ በአስገድዶ መድፈር ወንጀል እና በከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከስሶ በሁለቱም ጥፋተኛ ቢባል፣ ለሁለቱም ወንጀሎች በተደነገጉት ቅጣቶች ተደምሮ ይቀጣል ሆኖም ጣሪያው ከ30 ዓመት አይበልጥም።

## አንቀጽ 191

ይህ አንቀጽ ቀደም ሲል ከነበሩት ሁለት ንዑሳን አንቀጾች በተጨማሪ አንድ ሌላ ንዑስ አንቀጽ (3) ተጨምሮ አንድ ወንጀለኛ ለተለያዩ ጥፋቶች በተለያዩ ፍ/ቤቶች ወይም በተለያዩ ፍ/ቤቶች የተለያዩ ቅጣቶች በወሰኑበት የቅጣት አወሳሰን መርሁ በአንቀጽ 189 ላይ



ethcriminalawnetwork.com

በተመለከተው አኳኋን እንደሚሆን ተደንግጓል። ይህንን ተፈጻሚ ለማድረግም የተሟላ የመረጃ ሥርጭት እንዲኖር ማድረግ አግባብነት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 196

ይህ አንቀጽ አንድ ወንጀለኛ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ከተባለ እና ቅጣት ከተወሰነበት በኋላ ቅጣቱ ሳይፈፀም እንደታገድ የሚደረግበትን ሁኔታ የሚደነግግ ነው። በሥራ ላይ ባለው ሕግ ወንጀለኛው ቀደም ሲል ወንጀል የሌለው ቢሆንም ባይሆንም ሊታገድ የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ ይደነግጋል። አሁን በተሻሻለው ረቂቅ ላይ ግን ወንጀለኛው ቀደም ሲል ወንጀል ፈጽሞ የነበረ ከሆነ ቅጣቱ ሊታገድለት የማይገባ መሆኑ ስለታመነበት "ከዚህ በፊት የተቀጣ ቢሆንም ባይሆንም" የሚለው እንዲሠረዝ ተደርጓል።

## አንቀጽ 198

ይህ አንቀጽ ደግሞ ቅጣቱ ከተወሰነ በኋላ ሊታገድ የማይችልበትን ሁኔታ የሚደነገግ ነው ስለሆነም ከላይ በአንቀጽ 196 ሥር በተገለፀው ምክንያት ማሻሻያ ተደርጎበታል። ስለሆነም ቀደም ሲል ወንጀል ፈጽሞ የተቀጣ ሰው ከሆነ ወይም ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ቢሆንም አሁን የተከሰሰበት ወንጀል ከሶስት ዓመት በሚበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በጽኑ እሥራት ቅጣት የሚያስቀጣው ከሆነ ቅጣቱ እንደማይታገድ ተገልጾ ተደንግጓል።

## አንቀጽ 225

ይህ አንቀጽ ወንጀል ተፈጽሞ በሕጉ ላይ የተገለጸው ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ በይርጋ የሚታገድበትን ሁኔታ የሚደነግግ ነው። ስለሆነም በዚህ አንቀጽ ውስጥ ቀደም ሲል ያልነበረ "በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር" የሚል ገብቷል። ይህንንም ማስገባት ያስፈለገው አንዳንድ ወንጀሎች በይርጋ የማይታገዱ በመሆናቸውና ይህም በሕገ መንግሥታችን በአንቀጽ 28(1) ላይ እንደተደነገገው እና በሌሎችም አለማቀፍ ሰነዶች ውስጥ በስብዕና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በይርጋ የማይታገዱ በመሆናቸው ይህንኑ ለማመልከት ታስቦ ነው።


ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 226

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 225 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች ወንጀሎች ላይ ያለውን የክስ ይርጋ ቀሪነት በተመለከተ ቀደም ሲል ከነበረው ሕግ በተለየ ሁኔታ ከፍ እንዲል ተደርጓል። ይህም የቅጣቱን ጣሪያ ከፍ ማለት ተከትሎ የተደረገ ነው። በዚህም መሠረት፤

በ' ሀ' ላይ ሃያ አምስት ዓመት የነበረው ወደ 30 ዓመት፣ በ'ለ' ላይ ሃያ ዓመት የነበረው ወደ 25 ዓመት፣ በ' ሐ' ላይ አሥራ አምስት ዓመት የነበረው ወደ 20 ዓመት፣ በ'መ' ላይ አሥር ዓመት የነበረው ወደ 15 ዓመት፣ በ'ሠ' ላይ አምስት ዓመት የነበረው ወደ 10 ዓመት፣ በ'ረ' ላይ ሦስት ዓመት የነበረው ወደ 5 ዓመት፣ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

## አንቀጽ 232

በዚህ አንቀጽ ላይ የሠፈረውን የፍትሐብሔር ይርጋ በተመለከተ የፍትሐ ብሔር ሕጉና የወንጀል ሕጉ ሲነጻጸሩ በአብዛኛዎቹ ወንጀሎች ላይ ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ከፍተኛ የይርጋ ጊዜ ( 10 ዓመት) ይልቅ የወንጀሉ የይርጋ ጊዜ ከፍ ስለሚል አላስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ተሰርዟል።

## አንቀጽ 233

ይህ አንቀጽ ለአንድ ወንጀል ቅጣት ከተወሰነ በኋላ በተለያየ ምክንያት ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር በይርጋ የሚታገድበትን ሁኔታ የሚደነግግ መርህን ይዟል። ስለሆነም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 28(1) ላይ በይርጋ የማይታገዱ ቅጣቶች ስላሉ ይህንኑ እንዲያካትት ታስቦ " በሕግ በሌላ አኳኋን በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር" የሚል መንደርደሪያ በአንቀጹ ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል። ከዚህም ሌላ የጥንቃቄ እርምጃዎች ከዋናው ቅጣት ጋር እንደሚጠቃለል ሲደነገግ ያለዋነኛ ቅጣት የጥንቃቄ እርምጃ ቢወሰን ምን ይሆናል። የሚለውን የቀድሞው ሕግ ስለማይመልስ ይህን ለማካተት በንዑስ አንቀጽ (1) ሁለተኛ ፓራግራፍ መጨረሻ ላይ " የጥንቃቄ እርምጃዎች ያለዋነኛ ቅጣት በሚወሰኑበት ጊዜ የዚህ ሕግ አንቀጽ 234 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ" የሚል እንዲገባና ጉዳዩ በአንቀጽ 234 ሥር እንዲካተት ተደርጓል።


ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 234

ይህ አንቀጽ በአንቀጽ 233 ላይ የተቀመጠው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ቅጣቶች ሳይፈጸሙ ቢቀሩ በይርጋ የሚታገዱበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው። ስለሆነም በሕጉ ላይ የቅጣት ጣሪያውን ከፍ ማለት ተከትሎ የሚከተሉት ለውጦች ተደርጎበታል።

- በ' ሀ' ላይ ከ30 ዓመት ወደ 35 ዓመት ከፍ ብሏል፤
- በ 'ለ' ላይ ከ20 ዓመት ወደ 25 ዓመት ከፍ ብሏል፤
- በ 'ሐ' ላይ ከ10 ዓመት ወደ 15 ዓመት ከፍ ብሏል፤
- በ 'መ 'ላይ በተናጠል የሚወሰን የጥንቃቄ እርምጃን ጨምሮ እንዲሸፍን ከተደረገ በኋላ የነበረው 5 ዓመት እንዳለ ሆኖ ተቀርጿል።

## አንቀጽ 239

በዚህ አንቀጽ ላይ "pardon" ለሚለው ቃል " ምህረት" ተብሎ የተሰጠው ትርጉም " ይቅርታ" በሚል ቃል ተተክቷል። ይህም የሆነበት ምክንያት በአንቀጽ 240 ላይ ከተመለከተው ጋር አሻሚ እንዳይሆን ለመለየት እና "ይቅርታ" የሚለው ቃልም በህገ መንግሥቱ ላይ ለፕሬዚዳንቱ ከተሰጠ ሥልጣን ጋር ስለሚጣጣም ነው። በአንቀጽ 116 መሠረት የሞት ቅጣትን ማጽናት በተመለከተ ለፌዴራሉ ርዕሰ ብሔር የተሰጠ መሆኑ ቢታወቅም የፍርድ ቅጣቶችንም ይቅርታ ማድረግ ከሞት ቅጣት በመለስ ያሉ የፍርድ ቅጣቶችን ስለሚያካትት በተለይ በክልል ፍ/ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎችን በተመለከተ ይቅርታ የሚያደርገው ማነው? የሚለው አከራካሪ ነጥብ ተነስቶ ነበር። ጉዳዩ ብዙ ካወያየ በኋላ አንዳንድ የክልል ሕገ መንግሥቶች በታዩበት ጊዜ ይህ ሥልጣን ለክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች የተሰጠ በመሆኑ፤ የመከላከያ አባላትን በሚመለከት በተለየ አካል የሚታይ በመሆኑ እና በአንዳንድ አገሮች ደግሞ ለሚሰየም አንድ አካል የሚሰጥ በመሆኑ፤ እንዲሁም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 28 መሠረት ይቅርታ የማይሰጥባቸው ወንጀሎች ስላሉ፤ ይህንን ሁሉ ከግምት በማስገባት አንቀጽ 239(1) በረቂቁ ላይ በተመለከተው ሁኔታ ተቀርጿል። ሆኖም አከራካሪ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።


ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 240

በፊተኛው አንቀጽ ላይ በፍርድ የተወሰነ ቅጣትን ይቅር ማለት የሚቻለው በይቅርታ መልክ መሆኑ ተጠቅሶ ስለተረቀቀ አንቀጽ 240 ምህረት ብቻ ተብሎ ርዕስ ተሰጥቶታል ይህም ምህረት የሚሰጠው በፍርድ ውሳኔ ባላገኙ ጉዳዮች ላይ ስለሆነ አሠጣጡ በየትኛው የመንግሥት አካል ውሳኔ ወይም በየትኛው የመንግሥት አካል በሚወጣ ድንጋጌ መሆኑ በህገ መንግሥቱ ላይ ባለመገለጹ ምህረት ሰጭውን መጥቀስ አልተቻለም ይህም በመሆኑ ይህ ጉዳይ አከራካሪ ነበር። ስለዚህ ምህረት አሰጣጥን የሚደነግግ ዝርዝር ህግ እንደሚያስፈልግ በሚጠቁም መልክ እና በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 28 መሠረትም ምህረት የሚደረግላቸው ወንጀሎች መኖራቸውን ባመለከተ መልኩ ረቂቁ ተዘጋጅቷል።

# III. በሕጉ ልዩ ክፍል ላይ የተደረጉ ለውጦች

ይህ ክፍል ወንጀሎችን እና ለየወንጀሎቹ የሚጣለውን ቅጣት የሚደነግግ የሕጉ ልዩ ክፍል ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ የተደረጉ ዋና ዋና ለውጦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 1. በአገር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ( ከአንቀጽ 248-295)

### 1.1. አጠቃላይ

በዚህ ርዕስ ሥር በአጠቃላይ ካለንበት ሥርዓት ጋር የማይሄዱ ስሞች፣ ስያሜዎች እና አነጋገሮች ተሰርዘው አግባብ ባላቸው በሌሎች ስሞችና ስያሜዎች ተተክተዋል። ለምሳሌ ንጉሠ ነገሥቱ፣ ንጉሣውያን ቤተሰቦች፣ ዙፋን እና ዙፋን አወራረስ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት የሚሉት ተሰርዘው እንደአግባቡ በሌሎች ተተክተዋል። ዝርዝሩ በየአንቀጹ ላይ ተመልክቷል።

- ሕገ መንግሥት እና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት የሚለው አነጋገር የፌዴራሉንና የክልል ሕገ መንግሥትንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን በሚያጠቃልል ሁኔታ ተስተካክሏል።
- በጣም አነስተኛ የነበሩ የቅጣት ሁኔታዎች አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ ከፍ እንዲሉ ተደርጓል።


ethcriminalawnetwork.com

## 1.2 ዝርዝር ለውጦች

### አንቀጽ 248

ይህ አንቀጽ ቀደም ባለው ሕግ ውስጥ ለንጉሠ ነገሥቱ እና ለንጉሣውያን ቤተሰቦች ጥበቃ ያደርግ ነበር። በአዲሱ ረቂቅ ላይ ግን ለአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ብቻ ጥበቃ የሚያደርግ ሆኖ ተቀርጿል። ለአንድ አገር ርዕሰ ብሔር በሕግ ጥበቃ ማድረግ በብዙ አገሮች ሕጎች ውስጥ የተለመደ ስለሆነ በእኛም ሕግ ውስጥ ይኸው ተደርጓል።

### አንቀጽ 249

በሥራ ላይ ያለው ሕግ ጥበቃ የሚያደርገው ለዙፋን አወራረስ ነበር። አሁን ከቀረበው ረቂቅ ላይ ግን ከርዕሰ ብሔሩ በተጨማሪ ጥበቃ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ባለሥልጣኖች የሚጠብቅ ሆኖ ተቀርጿል። በዚሁ መሠረት ለአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ፣ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ፕሬዚዳንት፣ ለፓርላማ አፈጉባዔ፣ ለክልል መስተዳድር እና ለሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጥበቃ የሚያደርግ ድንጋጌን ይዟል።

### አንቀጽ 250

ቀደም ሲል የነበረው አንቀጽ የንጉሠ ነገሥታዊ ሥርዓቱን እና አካላቱን የሚጠብቅ ነበር። በአሁኑ ረቂቅ ላይ ደግሞ በፌዴራልም ሆነ በክልል ሕገ መንግሥት የተመሠረተውን ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት በሚጠብቅ ሁኔታ ተቀርጿል። ቀደም ሲል በነበረው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ለ) ላይ የተዘረዘሩትን አካላት በሚመለከት "በሕገ መንግሥቱ የተመሠረተውን ሥርዓት" በሚለው ስለሚሸፈን ከዚያ በመለስ ያለው ደግሞ በአንቀጽ 251 ላይ ስለተሸፈነ በአዲሱ ረቂቅ ላይ ዝርዝራቸው አልተጠቀሰም።

### አንቀጽ 251

ይህ አንቀጽ ከፌዴራል ሥርዓተ መንግሥታችን ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በፌዴራል እና በክልል ሕገ መንግሥት ሥልጣን የተሰጣቸውን አካላት እና ባለሥልጣኖች የሥራ አካሄድ በማደናቀፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚሸፍን ሁኔታ ተቀርጿል። አካላት ሲባል ሕግ አውጭውን፣ ሕግ አስፈጻሚውን እና የዳኝነት አካላትን የሚመለከት ሲሆን ባለሥልጣኖች ሲባልም የነዚህኑ አካላት ባለሥልጣኖች የሚመለከት ይሆናል።


ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 252 (ሀ)

ይህ አንቀጽ አዲስ አንቀጽ ነው። በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ በተበታተነ ሁኔታ የሚገኘውንና ነገር ግን ግልጽ ባለመሆኑ በአፈጻጸም ረገድ ያጋጠሙ የነበሩ ችግሮችን እንዲፈታ እና አገራችን በአጸደቀችው ሽብርተኝነትን ለመከላከል የወጣውን የአፍሪካ የጸረ-ሽብርተኝነትን ኮንቬንሽን አፈጻጸም ለማመቻቸት የሚያስችል ነው። ከኮንቬንሹኑ ውስጥ የተወሰደ ሆኖ ሽብርተኝነትንና በዚሁ ወንጀል በተለያየ ደረጃ የሚደረግ ተከፋይነትን በሚያጠቃልል ሁኔታ ተቀርጿል። በዝርዝሩ ውስጥ እንደተመለከተውም ወንጀሉ የሚፈጸምባቸውን ሰዎችና አካላት፤ ወንጀሉ የሚፈጸምበትን ዓላማ እና ለዚህም የሚጣለውን ቅጣት ድንጋጌው ያሳያል።

## አንቀጽ 253

በዚህ አንቀጽ ላይ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት በኃይል ወይም ሕገ መንግሥቱን በሚፃረር ሁኔታ የሕዝብን አንድነት ለማፍረስ ወይም ከፌዴሬሽን ተከፍሎ ወይም ተነጥሎ እንዲሄድ ማድረግን ይቀጣ ነበር። የዚህ ሕግ ተፈጻሚነት አሁን ካለው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 ጋር የተጣጣመ ነው? አይደለም ? የሚል ሀሳብ ተነስቷል። የአሁኑ ሕገ መንግሥትም ቢሆን በኃይል፣ በማስገደድ ወይም ሕገ መንግሥቱን በሚፃረር ሁኔታ የሚፈጸምን የመገንጠል ጥያቄ የሚያስተናግድ ስላልሆነ የድንጋጌው ተፈጻሚነት አካራካሪ አልሆነም። ስለሆነም አስፈላጊው ማስተካከያ ከተደረገለት በኋላ ተቀባይነትን አግኝቷል።

## አንቀጽ 256

ይህ አንቀጽ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት ንጉሠ ነገሥቱን ወይም የአገሪቱን ባለሥልጣኖች የደፈረን ወይም ያዋረደን ሰው ይቀጣ ነበረ።

ነገር ግን የድንጋጌው ይዘት አሁን ካለንበት የዲሞክራሲ ሥርዓት አንፃር ሲታይ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ የሕዝቦችን ሀሳብን የመግለጽ እና የመንግሥት አሠራርን የመተቸት መብት ሊነፍግ ይችላል የሚል ሥጋት አሳድሯል። ስለሆነም ድንጋጌው ለአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ብቻ ጥበቃ የሚያደርግ እንዲሆን እና ከዚህ ውጭ ያሉ ባለሥልጣኖች ግን አሠራራቸውን በተመለከተ ሕዝቡ መተቸት መቻል ስላለበት ከመደበኛው ሁኔታ ወጣ ተብሎ የስም ማጥፋት ወንጀል ከተፈጸመባቸው እንደማናቸውም ሰው በሕጉ ከአንቀጽ 580-588 በተደነገገው መሠረት ክስ ሊያቀርቡ ስለሚችሉ በነዚሁ ድንጋጌዎች የሚሸፈኑ ይሆናሉ ተብሎ ታምኖበት በዚሁ ታልፏል።


ethcriminalawnetwork.com

የፍርድ ቤት ባለሥልጣኖችን በሚመለከትም በሕጉ አንቀጽ 443 መሠረት ማስተናገድ ስለሚቻል በዚህ አንቀጽ ሥር አልተሸፈኑም።

### አንቀጽ 274።

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ" ከኢትዮጵያ ጋር ስላማዊ የሆነ ወዳጅነት ባለው አገር ላይ" የሚለው ተሰርዟል። ምክንያቱም አገራችን በወዳጅም ሆነ ወዳጅ ባልሆነ አገር ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን የመከላከል ግዴታ ስላለበት ነው።

## 2. ወታደራዊ ወንጀሎች ( ከአንቀጽ 296-353)

### 2.1. አጠቃላይ

በዚህ ርዕስ ስር የሚከተሉት ዋና ዋና ለውጦች ተደርገዋል።

- ቅጣታቸው በጣም አነስተኛ የነበሩ አንዳንድ ወንጀሎች ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል።
- ርዕሱ በዋናነት ወታደሮችን የሚመለከት ስለሆነ "ማንም ሰው"የሚለው አባባል አግባብ በሆነው ቦታ ሁሉ "ማናቸውም የመከላከያ ሠራዊት አባል" ተብሏል።
- " ጦር ሥራዊት" ወታደሮች" የሚሉት ቃላት " የመከላከያ ሠራዊት አባል" በሚል ተተክቷል።
- ሁለት አዲስ አንቀጾች እንዲገቡለት ተደርጓል።

### 2.2. ዝርዝር ለውጦችን በሚመለከት

በዚህ ርዕስ ሥር የሚከተሉት ዋና ዋና ዝርዝር ለውጦች ተደርገዋል።

### አንቀጽ 309

በዚህ አንቀጽ ይዘት ውስጥ አንድ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) እንዲገባ ተደርጎ በማዕረግ እኩያ የሆነን ባልዳረባ መስደብ ወይም በዚሁ ላይ የእጅ እልፊት መፈጸም የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል። ይህም የሆነበት ምክንያት በአንቀጽ 305 ላይ በበታች ላይ፤ በአንቀጽ 310


ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 360 እና 361

እነዚህ አንቀጾች የሚደነግጉት የመንግሥት ግብርን አለመክፈልንና እንዳይከፈል ማነሳሳትን ለመቅጣት ነው። ነገር ግን ጉዳዩ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ሳለ በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ የተደነገገው ቅጣት በጣም አነስተኛ በመሆኑ ቅጣቱ ተገቢ ነው ተብሎ በታመነበት ሁኔታ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

## 4. በታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣ ማህተሞች፣ቴምብሮች ወይም መሣሪያዎች ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች ( በአንቀጽ 366-382)

በዚህ ርዕስ ሥር የሚከተሉት ዋና ዋና ለውጦች ተደርገዋል።

### 4.1. አጠቃላይ

በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ የዋስትና እና የግዴታ ሰነዶች(Bond and securities) እንደ ሰነድ ተቆጥረው ከሌሎች የንግድ ሰነዶች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጥበቃ ተደርጎላቸው ነበረ። ነገር ግን በተሻሻለው ረቂቅ ላይ እንደገንዘብ ተቆጥረው ለገንዘብ የተደረገው ጥበቃ ሁሉ ለእነዚሁም እንዲሰጥ ተደርጓል። ስለሆነም ከአንቀጽ 383-392 ካሉት አንቀጾች ውስጥ ተሰርዘው ከአንቀጽ 366-382 ባሉት አንቀጾች ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል። ምክንያቱም በነዚህ ሰነዶች በሚፈጸም ወንጀል በመንግሥት ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ በሌሎች ሰነዶች ላይ ከሚፈጸም ወንጀል ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ በመሆኑ ነው።

### 4.2 ዝርዝር ለውጦች

#### አንቀጽ 371 እና 372

በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ ሁለቱም አንቀጾች በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመንግሥት ማህተሞች ጥበቃ ያደረጉ ነበረ። በተሻሻለው ረቂቅ ላይ ግን አንቀጽ 371 በጠቅላላው የመንግሥትን ማህተም ብቻ የሚጠብቅ፣ አንቀጽ 372 ደግሞ ሌሎች ማህተሞችን( የግልን ጨምሮ) የሚጠብቅ እንዲሆን ተደረጎ ቅጣቱም እንደየአግባቡ እንዲወሰን ተደርጎ ተቀርጿል።


ethcriminalawnetwork.com

ላይ ደግሞ በበላይ አለቃ ላይ የሚፈጸሙ ተመሳሳይ ወንጀሎች የሚያስቀጡ ሆነው ሳለ በእኩያ ላይ የሚፈጸም ወንጀልን የሚሸፈን ድንጋጌ ባለመኖሩ ነው።

## አንቀጸ 327 (ለ)

ይህም አንቀጽ ቀደም ሲል ያልነበረ እና አዲስ ነው። ድንጋጌው የተሰው ( የሞቱ) ወይም የቆሰሉ ጓዶችን ጥሎ በመሄድ ለጠላት አሳልፎ በመስጠት በአገርና በሠራዊቱ ሞራል ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ወንጀሎችን የሚቀጣ ድንጋጌ ነው። ይህም ከተሞክሮ የተገኘውን ለማካተት ታስቦ የተደረገ ነው።

## 3. በመንግሥት ኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች (ከአንቀጽ 354-365)

በዚህ ርዕስ ሥር የሚከተሉት ዋና ዋና ለውጦች ተደርገዋል።

## አንቀጽ 354

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ ጥበቃ የተደረገላቸው የገንዘብ ወይም የኢኮኖሚ ጥቅሞች ዝርዝር የተሟላ ካለመሆኑም በላይ ግልጽነት የሚጎድላቸው በመሆኑ አጠቃላይ በሆነ አነጋገር ጥበቃ ማድረግ በማስፈለጉ በሕግ መሠረት ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል የአገርን ገንዘብ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ለመጠበቅ እና ለመቆጣጠር የወጡ ሕጎች በተጣሱ ጊዜ ቅጣት የሚወሰንበትን መርህ ረቂቁ አስቀምጧል። ስለሆነም ከመደበኛው ሕግ ውጭ በደንብ መተላለፍ ድንጋጌ የሚታዩ ጉዳዮችም በንዑስ አንቀጽ (2) ላይ ተገልጸዋል።

## አንቀጽ 358

ይህ አንቀጽ የከበሩ ማዕድናትን በሚመልከት ሕገ ወጥ ንግድ በተደረገ ጊዜ ቅጣትን የሚጥል ቢሆንም ለሕጉ አፈጻጸም የተከለከሉና የተፈቀዱ ማዕድኖችን የሚደነግግ ሌላ ራሱን የቻለ ሕግ እንደሚወጣ ግንዛቤ በመወሰድ ባለበት ሁኔታ እንዲሆን ተደርጓል። አለበለዚያ አሁን ባለበት ሁኔታ ( ሌላ ሕግ ሳይኖር) ይህንን አንቀጽ ተፈጻሚ ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታ እንዳለ በተግባር የታየ ጉዳይ ነው።


ethcriminalawnetwork.com

### አንቀጽ 360 እና 361

እነዚህ አንቀጾች የሚደነግጉት የመንግሥት ግብርን አለመክፈልንና እንዳይከፈል ማነሳሳትን ለመቅጣት ነው። ነገር ግን ጉዳዩ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ሳለ በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ የተደነገገው ቅጣት በጣም አነስተኛ በመሆኑ ቅጣቱ ተገቢ ነው ተብሎ በታመነበት ሁኔታ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

## 4. በታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣ ማህተሞች፣ቴምብሮች ወይም መሣሪያዎች ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች ( በአንቀጽ 366-382)

በዚህ ርዕስ ሥር የሚከተሉት ዋና ዋና ለውጦች ተደርገዋል።

### 4.1. አጠቃላይ

በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ የዋስትና እና የግዴታ ሰነዶች(Bond and securities) እንደ ሰነድ ተቆጥረው ከሌሎች የንግድ ሰነዶች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጥበቃ ተደርጎላቸው ነበረ። ነገር ግን በተሻሻለው ረቂቅ ላይ እንደገንዘብ ተቆጥረው ለገንዘብ የተደረገው ጥበቃ ሁሉ ለእነዚሁም እንዲሰጥ ተደርጓል። ስለሆነም ከአንቀጽ 383-392 ካሉት አንቀጾች ውስጥ ተሰርዘው ከአንቀጽ 366-382 ባሉት አንቀጾች ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል። ምክንያቱም በነዚህ ሰነዶች በሚፈጸም ወንጀል በመንግሥት ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ በሌሎች ሰነዶች ላይ ከሚፈጸም ወንጀል ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ በመሆኑ ነው።

### 4.2 ዝርዝር ለውጦች

#### አንቀጽ 371 እና 372

በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ ሁለቱም አንቀጾች በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመንግሥት ማህተሞች ጥበቃ ያደረጉ ነበረ። በተሻሻለው ረቂቅ ላይ ግን አንቀጽ 371 በጠቅላላው የመንግሥትን ማህተም ብቻ የሚጠብቅ፣ አንቀጽ 372 ደግሞ ሌሎች ማህተሞችን( የግልን ጨምሮ) የሚጠብቅ እንዲሆን ተደረጎ ቅጣቱም እንደየአግባቡ እንዲወሰን ተደርጎ ተቀርጿል።


ethcriminalawnetwork.com

## 5. በሕዝብ ጥቅምና ማህበራዊ ኑሮ ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ( ከአንቀጽ 383-409)

በዚህ ክፍል ውስጥ የተደረገው ዋና ለውጥ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 4.1 ላይ እንደተገለጸው በዚህ ክፍል ሥር ጥበቃ ተሰጥቷቸው የነበሩ የግዴታና የዋስትና ሰነዶች ተሰርዘው ለሌሎች ሰነዶች ብቻ ጥበቃ ተደርጓል።

## 6. በመንግሥት ሥራ ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ( ከአንቀጽ 410-437)

በዚህ ርዕስ ሥር የሚከተሉት ጠቅላላ ለውጦች ተደርገዋል።

### 6.1 አጠቃላይ

በዚህ ክፍል ውስጥ ከዚህ በፊት ባሉት ክፍሎች እና አንቀጾች ውስጥ ባልታየ ሁኔታ የአንቀጽ መፋለስና ይህም ባስከተለው ሁኔታ በውስጡ የነበሩ ምዕራፎች፣ ክፍሎችና ንዑስ ክፍሎች ተሰርዘው አንቀጾች ከ410-437(ሀ) በተከታታይ እንዲቀመጡ ተደርጓል።

### 6.2 ዝርዝር ለውጦች

#### አንቀጽ 410

በዚህ አንቀጽ ሥር የመንግሥት ሠራተኛ ማነው? የመንግሥት ሥራስ የሚባለው የቱ ነው? የሚሉ ችግሮችን ሲያስነሳ የነበረ አንቀጽ ነው። አሁን በተረቀቀው አንቀጽ ላይ ይህንን ችግር ይቀርፋል ተብሎ በርዕሱ ሥር የመንግሥት ሥራና የሕዝብ አገልግሎት ሁሉ እንደሚሸፈን እና የመንግሥት ሥራን እና የሕዝብ አገልግሎትን ለመተርጎም ተሞክሯል ( ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ) ። ስለሆነም በንዑስ አንቀጽ (3) ላይ እንደተመለከተው የመንግሥት ሥራን ወይም የሕዝብ አገልግሎት ሥራን የሚያከናውን ሰው ሁሉ(እንደመንግሥት ሠራተኛ ተቆጥሮ) በዚህ ርዕስ የሚሸፈን ሆኗል። በመሆኑም በእያንዳንዱ ተከታይ አንቀጽ ውስጥም ድንጋጌዎቹ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ተሻሽለው ተቀርጸዋል።

ምናልባት አዲስ ሀሳብ በመሆኑ አከራካሪ የሚሆነው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግሉ ዘርፍ እንዴት እንደመንግሥት መሥሪያ



ethcriminalawnetwork.com

ቤት ይቆጠራሉ የሚለው ሀሳብ ነው ( 410(2)። ሀሳቡ እንዲካተት ያስፈለገበት ምክንያት ዛሬ NGO በብዙ አገሮች ውስጥ በሕዝብ ስም ከመንግሥት በሚሰጥ ድጎማ ጭምር በርካታ የሕዝብ ሀብት የሚያንቀሳቀሱና በአግባቡ የማይጠየቁ ከሆነ ከፍተኛ የሕዝብ በደል ሊያደርሱ የሚችሉ በመሆናቸው፤ የግሉን ዘርፍ በተመለከተም ቀደም ሲል በመንግሥት ብቻ ይሰጡ የነበሩ የባንክ፣ የኢንሹራንስ፣ የመብራት፣ የውሃ፣ የስልክ፣ የትራንስፖርት እና የፖስታ አገልግሎቶች ( ሌሎችም ሊኖሩ ይችላሉ) በግል ዘርፍ የሚሰጡበት ሁኔታ እየተፈጠረ ስለሆነ እና ተገቢው ትኩረት ካልተሰጣቸው በሕዝብ ላይ ከፍተኛ በደል ሊደርስ ስለሚችል ነው።

## አንቀጽ 411

ይህ አንቀጽ ቀደም ሲል የነበረውን ቦታ እንደያዘ ይዘቱ በፊት ከነበረው አገላለጽ ለየት ባለ ሁኔታ የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ክስ በጣምራ ሊቀርብ የሚቻል መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ ተቀርጿል። ይህም ወጪን እና የክስ መንተት ሂደትን ሊያስቀር ይችላል ተብሎ ይታመናል።

## አንቀጽ 412

ይህ አንቀጽ በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ በአንቀጽ 425 እና 437 ላይ የሠፈሩትን ሀሳቦች በማጠቃለል እና የጉቦን ዘመናዊ ትርጉም ይዞ እንዲቀረጽ ተደርጓል። በዚህም ጉቦ መስጠትም ሆነ መቀበል በዚህ አንቀጽ ውስጥ ተጠቃልለው ተመሳሳይ ቅጣት የሚያስቀጡ ከመሆናቸውም በላይ ከዚህ በተጨማሪ የጉቦ ወንጀሎች የሕግ ሰውነት ባለው አካል በተፈጸሙ ጊዜ እንደሚያስቀጡ እና በዚሁ ወንጀል የተገኘውን ጥቅም ሕጋዊ ፣ ለማድረግ ( money Laundering)፣ ለማሸሽ፣ ወይም ለመጠቀም መሞከር እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል። ቅጣቱም ከፍተኛና በጣምራ የሚፈጸም እንዲሆን ተደርጓል።

## አንቀጽ 413

የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በሥራ ላይ ባለው ሕግ በአንቀጽ 423 ላይ የነበረው ድንጋጌ ይዘት ነው። ከዚህ በላይ በአንቀጽ 412 (1) ላይ ከሰፈረው ድንጋጌ የሚለይበት የበፊቱ ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም በመቀበል ሕገ ወጥ ሥራ መሥራትን የሚመለከት ሲሆን በዚህኛው አንቀጽ ላይ የተደነገገው ግን ሕጋዊውን ሥራ ለመሥራት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መጠየቅን ወይም መቀበልን የሚመለከት ነው። ከዚህም በተጨማሪ በግልጽ ባይጠየቅም በተዘዋዋሪ መንገድ ማለትም ያለአግባብ በጊዜው ባለመወሰን ጉዳይን ይዞ ማቆየትና ባለጉዳይን ማጉላላት ( ማመላለስ) ጥቅም እንደመጠየቅ ተቆጥሮ እንደሚያስቀጣ


ethcriminalawnetwork.com

በንዑስ አንቀጽ (2) ላይ ተደንግጓል። ይህ ድንጋጌ እንዲገባ የተደረገው በተግባር የሚታይ ከፍተኛ ችግር በመሆኑ ነው።

## አንቀጽ 414

ይህ አንቀጽ አዲስ ድንጋጌ ሲሆን በአንቀጽ 412 እና 413 በተመለከቱት ወንጀሎች ውስጥ በሰጪነትም ሆነ በተቀባይነት ድርጊት ውስጥ በወንጀል ተካፋይ የነበረ ሰው ወንጀሉ ለፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት ለሚመለከተው አካል በመጠቆም ድርጊቱ ተጋልጦ ለሕግ እንዲቀርብ ካደረገ ከመክሰስ ነፃ የሚሆንበት ሁኔታ ተደንግጓል። ይህም በስውር የሚፈጸመውን የጉቦና የመደለያ ወንጀል ለማጋለጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ታምኖበታል። ጠቋሚው እንዳይከሰስ የማድረግ ሥልጣንም የፌደራሉ የፍትሕ ሚኒስቴር ( በፌዴራል ጉዳይ ላይ) እና የክስ የፍትሕ ቢሮ ኃላፊ ( በክልል ጉዳይ ላይ ) እንደሆነ ተመልክቷል።

## አንቀጽ 421

በዚህ አንቀጽ ላይ የሠፈረው ድንጋጌ በሥራ ላይ ባለው ሕግ በአንቀጽ 417 ላይ የነበረውን ሀሳብ ይዞ የተቀረጸ ነው። ነገር ግን በፊት ከነበረው ሀሳብ በተጨማሪ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ገብቶለት ሰውን የማስቃየቱ ወንጀል የተፈጸመው በባለሥልጣን ትዕዛዝ በሚሆንበት ጊዜ ትዕዛዙን ለሰጠው ባለሥልጣን የሚጣለው ቅጣት ከበድ ያለ እንዲሆን ተደርጎ ተደንግጓል።

## አንቀጽ 437 (ሀ)

ይህ አንቀጽ ቀደም ሲል ያልነበረ አዲስ አንቀጽ ሲሆን የድንጋጌው አስፈላጊነት ከአንቀጽ 410-437 በተደነገጉት አንቀጾች ውስጥ በተመለከቱ ወንጀሎች በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብ ወይም ጥቅም እንደሚወረስ እና ገንዘብ ወይም የተባለው ጥቅም ባይገኝ ተመጣጣኙ እንዲከፈል እንደሚደረግ የሚደነግግ አንቀጽ ነው።

## 7. በፍትሕ አስተዳደር ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች ( ከአንቀጽ 438-459)

በዚህ ርዕስ ሥር የሚከተሉት ለውጦች ተደርገዋል።

## አንቀጽ 441

በአንቀጽ 441 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት በሐሰት ሌላውን ሰው መወንጀል የሚያስቀጣው ከ5 ዓመት ጽኑ እሥራት ያልበለጠ ቅጣት ነበረ። ነገር ግን በሐሰት በተወነጀለው ሰው ላይ ምናልባት በሐሰት መወንጀሉ ሳይደረስበት ከ10 ዓመት


ethcriminalawnetwork.com

የበለጠ እና እስከሞትም የሚያደርስ ቅጣት ሊወሰን ይችላል። በተወንጀዩ ላይ ያለአገባብ የተወሰነው ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት የሐሰት ወንጀላው ከተደረሰበት የ5 ዓመቱ ቅጣት በቂ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የሐሰት ውንጀላ መሆኑ ከመታወቁ በፊት ቅጣቱ ከተፈጸመ እና ለማረም የማይቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረ አሳዛኝ ሁኔታን የሚያስከትል ድርጊት ነው። ስለሆነም በሐሰት ተወንጅሎ የተቀጣ ሰው ካለ ወንጀዩ በሌላ ሰው ላይ በሐሰት ባስወሰነው ቅጣት ልክ ሊቀጣ ስለሚገባው በዚሁ መሠረት ረቂቁ ተቀርጿል።

## አንቀጽ 443

በዚህ አንቀጸ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ ፍርድ ቤትን የመድፈር ወንጀል የተፈጸመው " በግልጽ ችሎት ያልሆነ እንደሆነ " የሚለው ሀረግ ግልጽነት ይጎድለው ነበረ። ምክንያቱም ከችሎት ውጭ ማለት ይሁን ወይም በችሎት ውስጥም ሆኖ ጉዳይ በማይስማበት ጊዜ ለማለት ይሁን ግልጽ አይደለም። ይህንን ችግር ለማስወገድ "ከችሎት ውጭ የሆነ እንደሆነ " ተብሎ ተስተካክሏል።

## አንቀጽ 451(ሀ)

ይህ አንቀጽ በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ የማይገኝ አዲስ አንቀጽ ነው። ይህ አንቀጽ ያስፈለገበት ምክንያት ዳኞች ተጠያቂነት በሌለው አኳኋን ሕግን በሚፃረር ሁኔታ ውሳኔ ሲሰጡ በሕግ የሚጠየቁበት ሥርዓት ባለመኖሩ ከፍተኛ በደሎች እየተፈጸሙ ይታለፋሉ። ዳኞች በሥራቸው ረገድ ከሕግ በስተቀር የሌላ አመራር ያለመቀበል ነፃነት እንዳላቸው ሁሉ የተሰጣቸውን ነፃነት ያለገደብ እንዳይጠቀሙበት የሚያደርግ ሕግ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ከኮሎምቢያ የወንጀል ሕግ የተወሰደ እና ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ እንዲቀረጽ ተደርጓ ዳኞች ሥልጣናቸውን ያለአገባብ ተገልግለውበት ከተገኙ የሚጠየቁበት ሁኔታ ተደንግጓል። ነገር ግን የዳኞች የሥራ አካሄድ ያለአገባብ እንዳይደናቀፍ በማሰብ ተሰራ የተባለው ጥፋት በቅድሚያ በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ታይቶ ጥፋት መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ክስ የሚቀርብ መሆኑ ተደንግጓል።

## አንቀጽ 451(ለ)

ከላይ በተገለጸው አኳኋን ዐቃቤ ሕግም ሥልጣኑን ያለአገባብ ከተገለገለ ልክ እንደዳኛው የሚጠየቅ ሆኖ ሥራው እንዳይደናቀፍ በማስብም ጉዳዩ በቅድሚያ በዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ታይቶ ጥፋት መሆኑ ሲረጋገጥ ክስ እንደሚቀርብ ተደንግጓል።


ethcriminalawnetwork.com

## 8. በሕዝባዊ ምርጫዎችና በድምጽ አሰጣጥ ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች( ከአንቀጽ 460-470)

### አንቀጽ 463

በዚህ አንቀጸ ላይ የተደረገው ለውጥ በሥራ ላይ ባለው ሕግ ላይ የነበረው ድንጋጌ በሙሉ የተሻሻለው ረቂቅ ሕግ ንዑስ አንቀጽ (3) እንዲሆን ሲደረግ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) አዲስ የገቡ ድንጋጌዎች ናቸው። እነዚህ ድንጋጌዎች በብዙ አገሮች የምርጫ ሕጎች ውስጥ የሚገኙ እና በእኛም ሕግ ውስጥ ቢካተቱ ይጠቅማሉ ተብለው የገቡ ናቸው። በዚህ መሠረት በንዑስ አንቀጽ (1) ላይ ማናቸውም እጩ ተመራጭ በሕግ ወይም በመመሪያ ከተፈቀደው ውጭ ለምርጫ ወጪ መሸፈኛ የሚሆን ገንዘብ ከማንም ሰው ወይም ቡድን ቢቀበል፣ ወይም የምርጫ ወጪ ሕግን በሚቃረን ሁኔታ ወጪውን ደብቆ አሳንሶ ያቀረበ እንደሆነ የሚያስቀጣ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀጽ (2) ላይ ደግሞ ማናቸውም ሌላ ሰው እጩ ተመራጩ ሳይፈቅድለት የተመራጩን ወጪ ለመሸፈን ገንዘብ የሰጠ፣ ያሰባሰበ ወይም የረዳ እንደሆነ እንደሚቀጣ ተደንግጓል። የዚህ ድንጋጌ አስፈላጊነት ከምርጫ ጋራ በተያያዘ የሚፈጸሙ የሙስና ሥራዎችን ለመከላከል የሚያገለግል ሲሆን የዚህን ሕግ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ እነዚህን የሚመለከቱ ሌሎች ሕጎች መውጣት እንዳለባቸው የሚያመለክቱ ናቸው።

## 9. በሕዝብ ደህንነት፣ ሰላምና ተረጋግቶ መኖር ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች ( ከአንቀጽ 471-487)

### አንቀጽ 475

ይህ አንቀጽ በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ 2 ንዑሳን አንቀጾች ብቻ የነበሩት ሲሆን በተሻሻለው ረቂቅ ላይ ግን (5) ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጎ የሚከተሉት ለውጦች ተደርገውበታል። በንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተመለከተው ወንጀል በቀላል ሁኔታ ከሚደረግ መሣሪያን በሕገወጥ መንገድ የማዘዋወር ወንጀል ለየት ባለ ሁኔታ አደገኛ ለሆኑ ሰዎች እያወቀ መሣሪያ በማናቸውም መንገድ ካስተላለፈ ከበድ ያለ ቅጣት እንዲጣልበት ተደርጓል። እንዲሁም ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ ከተፈጸመ በንዑስ አንቀጽ (3) ላይ እንደተመለከተው ቅጣቱ ከፍ ብሏል። ከዚህም በተጨማሪ በንዑስ አንቀጽ (5) ላይ እንደተመለከተው ከአንቀጽ 475 ውጭ በደንብ መተላለፍ የሚታዩ ጉዳዮች ፈቃድ ሳይኖር መሣሪያ መያዝ እና በነዚሁ ፈቃድ በሌላቸው መሣሪያዎች መገልገል ብቻ መሆኑ ተመልክቷል።


ethcriminalawnetwork.com

## 10. በሕዝብ፣ በመገናኛዎችና በማጓጓዣዎች ደህንነት ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች ( ከአንቀጽ 488-502)

የዚህ ክፍል ርዕስ በተዘረዘሩት አንቀጾች ውስጥ ከተካተቱ የወንጀል አይነቶች ጋር እንዲስማማ ከዚህ በላይ በተጻፈው አኳኋን ተሻሽሏል። ከዚህም በተጨማሪ የሚከተሉት ዋና ዋና ለውጦች ተደርገዋል።

### አንቀጽ 500 (ሀ)

ይህ አንቀጽ በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ ያልነበረ እና ነገር ግን ራሱን በቻለ የበረራ ደህንነት አዋጅ ውስጥ ተካትቶ የነበረውን ድንጋጌ አጠቃልሎ የያዘ አንቀጽ ነው። ስለሆነም አንቀጹ ሦስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጎ በበረራ ደህንነት አዋጁ ውስጥ በተለያዩ አንቀጾች ውስጥ የነበሩትን ድንጋጌዎች አጠቃልሎ ይዟል። ቅጣቱም በበረራ ደህንነት አዋጁ ውስጥ የነበረው እንዳለ ተወስዷል። ምክንያቱም የወንጀሉን ከባድነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

### አንቀጽ 502(ሀ)

ይህም አንቀጽ አዲስ ሲሆን በዚህ ርዕስ ሥር የተዘረዘሩትን ቅጣቶች ለማክበድ የገባ ነው። በመሆኑም የተገለጹት ወንጀሎች በሰው ሕይወት ላይ ሞትን፣ የአካል ጉዳትን፣ ወይም የጤና መጎዳትን አስከትለው ከሆነ ቅጣቱ ከፍ ብሎ በዕድሜ ልክ እሥራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ መሆኑ ተመልክቷል።

## 11. በጤና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች ( ከአንቀጽ 503-520)

የዚህ ክፍል ርዕስ በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ " በሕዝብ ጤና ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች " ይል ነበረ። ነገር ግን በዚህ ክፍል ውስጥ የተመለከቱት ወንጀሎች የሚሸፍኑት ከሕዝብ ጤና በተጨማሪ የሰብልን እና የእንስሳትን ጤንነት ጭምር በመሆኑ በአጭሩ "በጤና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች " ተብሎ ተቀይሯል። ከዚህ በተጨማሪ የሚከተሉት ዋና ዋና ለውጦች ተደርገዋል።

### አንቀጽ 503

በንዑስ አንቀጽ (2) ላይ ለተዘረዘሩት ወንጀሎች የተመደበው የአምስት ዓመት ቅጣት ከወንጀሉ አፈጻጸምና በተለይ አንዳንድ በሽታዎች ከሚያስከትሉት ጉዳት አንፃር በጣም አነስተኛ ሆኖ ተገምቷል።


ethcriminalawnetwork.com

ለምሳሌ አንድ ሰው በበቀል ስሜት፣ በክፋት ወይም በወራዳነት መንፈስ አንድን ሌላ ሰው ወይም ብዙ ሰዎችን በኤድስ በሽታ ቢበክል የሚያደርሰው ጉዳት ሞትን የሚያስከትል በመሆኑ ወንጀሉ የሚያደርሰው ጉዳት እና ለወንጀሉ የተደነገገው ቅጣት ተመጣጣኝ አይደለም። ስለሆነም የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ጥፋቱ እና ቅጣቱ ተመጣጣኝ ይሆኑ ዘንድ ቅጣቱ እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ወይም ሞት ሊሆን እንደሚችል ተደንግጓል።

## አንቀጽ 506

በዚህ አንቀጽ ውስጥ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት ወንጀል ተብሎ የተደነገገው ውሀን መበከል ብቻ ነበረ። በተሻሻለው ረቂቅ ላይ ግን አየርን መበከልም ወንጀል መሆኑ ተመልክቷል።

## አንቀጽ 510

በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት መርዛም ወይም የሚያፈዙ ነገሮችን ማውጣት ወይም መሥራት እንዲዘዋወሩ ማድረግ በሚል ርዕስ፤ እነዚህን ነገሮች ማዘዋወርን እና ለነዚሁ መጠቀሚያ የሚሆኑ ቦታዎችን ማመቻቸት ከሦስት ወር ባላነሰ ቀላል እሥራት እና እስከ 20 ሺህ ብር ያስቀጣ ነበረ። ከዚህ ሌላ ወንጀሉ የተፈጸመው በቡድን መልክ ከሆነ ወይም ሞያ አድርጎ ከሆነ ወይም ኃላፊነት ለሌላቸው ሰዎች በመሸጥ ከሆነ ቅጣቱ እስከ 5 ዓመት ጽኑ እሥራት እና 30 ሺህ ብር መቀጮ ያስቀጣ ነበረ።

ይህ ድንጋጌ በአፈጻጸም ረገድ ሁለት ችግሮችን አስከትሎ ነበረ። አንደኛው ከወንጀሉ አደገኛነት አንፃር ሲታይ ቅጣቱ በጣም አነስተኛ ነው። ሁለተኛው ችግር የሚያስቀጣው መርዛም ወይም የሚያፈዙ መድኀኒቶችን ማዘዋወር ብቻ ነበረ። አሁን ከሚታወቁት ዕጾች ውስጥ የሚያፈዙ ብቻ ሳይሆኑ የሚያነቃቁም እንዳሉ ይታወቃል። አይነታቸውም በአለም አቀፍ ደረጃ የታወቁትን ስያሜዎችም አልያዘም። ስለሆነም እነዚህን ችግሮች ለመቅርፍ በዚህ አንቀጽ ላይ የሚከተሉት ለውጥ ተደርገዋል።

1. ርዕሱ " መርዛም ወይም ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ ነገሮችን ስለማምረት፣ ስለመሥራት፣ ስለማዘዋወር እና ስለመጠቀም " ተብሎ ተሻሽሏል።

2. የሚያስቀጣውም በንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ እንደተመለከተው የተባሉትን ነገሮች ማዘዋወር ብቻ ሳይሆን፣ ዕፆቹን የዕፆቹን ወጤቶች፣ ዕፁን ማምረቻ መሣሪያዎች የዕፁን


ethcriminalawnetwork.com

መጠቀመያ መሣሪያዎችን ማምረት፣ ማዘዋወር፣ መስጠት፣ መሸጥ መለወጥ እንዲሆኑ ተደርጎ ሰፋ ተደርጓል። ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉበትን ሁኔታ ላለመከልከልም እነዚህ ነገሮች የሚያስቀጡት ፈቃድ ሳይኖር በተደረጉ ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል።

3. በንዑስ አንቀጽ (5) ላይ እንደተመለከተው ቅጣቱ አነስተኛ ቢሆንም ያለሀኪም ፈቃድ ዕፁን መጠቀምም እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል።

4. ለወንጀሉ የተደነገገው ቅጣትም የእሥራቱም ሆነ የገንዘብ ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

5. በንዑስ አንቀጽ (4) ላይ እንደተመለከተው ለዚሁ ወንጀል መፈጸሚያ የሚያገለግሉ ነገሮች እንደሚወረሱ ተመልክቷል።

6. በንዑስ አንቀጽ (6) ላይ እንደተመለከተው ደግሞ በዕፅ ዝውውር የተገኘ ገንዘብን በሥራ ላይ ማዋልና ሕጋዊ ለማድረግ መሞከር (money Laundering) እና በዚሁ ሥራ ተካፋይ መሆን እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል።

## 12. <u>የመግደል አደራረግና ዓይነቶች</u>
ከአንቀጽ 521-527

### <u>አንቀጽ 523</u>

በወንጀል ሥራ አፈጻጸም የሞራል ጠባይ አንዱና ዋነኛው ጉዳይ በመሆኑ፣ ከደንብ መተላለፍ በስተቀር፣ በተደነገጉት የወንጀል ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ አስቦ ወይም በቸልተኝነት የፈፀመ የሚል ቃል ወይም ሐረግ እየታከለበት ወንጀሉን በማቋቋም ረገድ፣ እንዲሁም በቅጣቱ መጠን አወሳሰን ላይ ልዩነት የማድረግ ሚና አለው። ከዚህ አንጻር የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 523 የግድያው አፈጻጸም አስቦ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ባለማመልከቱ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ አስቦ የሚል ቃል በረቂቁ ውስጥ ተካትቷል።

### <u>አንቀጽ 524</u>

በወ/መ/ሕግ ቁ.524 ውስጥ፣ ከዘራፊዎች ሲከላከል፣ወይም በሌሊት በቤቱ ወይም በግቢው ውስጥ በኃይል ወይም በተንኮል የገባበትን ለመመለስ ግድያ የፈፀመ ሰው፣ በሕጋዊ መከላከል እንደፈፀመ


ethcriminalawnetwork.com

እንዲቆጠር የሚገምት ድንጋጌ ተጨምሮ ንዑስ አንቀጽ 2 ሆኖ ተረቋል፤ ይህም የሆነበት ምክንያት እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች የሚፈጥሩት አደጋ፣ ይህንኑ ለመከላከል ወይም ለመቋቋም መልሶ ማጥቃትን የግድ ስለሚል እና፣ በዚህ መልክ በጥልቅ ስጋት መነሾ የሚፈፀመውን ግድያ ተከሳሽን ጥፋተኛ ነው ብሎ በቅጣት ማቅለል ብቻ ማየቱ ሚዘናዊ ስለማይሆን ነው።

## አንቀጽ 526

የወ/መ/ሕግ ቁ.526 ፤ በዚህ ድንጋጌ ውስጥ፣ በቸልተኝነት በሾፌሮች፣ በሐኪሞች ወ.ዘ.ተ ተግባር ብዙ ሕይወት እንደሚያልፍ ግንዛቤ መወሰዱን ለማመልከትና እነዚህም አጥፊዎች ሙያቸውን በከፍተኛ ጥንቃቄ ማከናወን ለመልካም ፈቃደኛነት ብቻ የተተወ ሳይሆን የጠበቀ የሕግ ተጠያቂነት ያለበት መሆኑን በውል ለይተው እንዲረዱት፣ በሚያስችል መልኩ በግልጽ ተብራርቶ እንዲደነገግ ሆኗል፤ በአንጻሩም የቅጣቱ መቅለል አጥፊዎችን ለማረም ሌሎችንም ለማስተማር የሚረዳ ስለአልሆነ፣ በረቂቁ ውስጥ ቅጣቱ ከፍ ተብሎ ተደንግጓል።

በንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተደነገገው በንዑስ ቁጥር 2 ላይ የተመለከተው ወንጀል ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሰው ሕይወት ሕልፈትን ካስከተለ ቅጣቱ በንዑስ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው የቅጣት መጠን ተደርጎ ተቀርጿል። ይህ ድንጋጌ በአንድ የወንጀል መሥራት ቸልተኝነት የተፈፀመውን እንዲሸፍን ሆኖ የተቀረጸ ነው። እንዲሁም መጠጥና የሚያፈዝ ንጥረ ነገርን በተመለከተ የተደነገገው በዚህ ሕግ አንቀጽ 50(2)መንፈስ ነው።

# 13 ጽንስን ስለማስወረድ

## አንቀጽ 533

በወ/መ/ሕግ ቁጥር 533 ላይ በመደፈር ወይም ከቅርብ ዘመድ ጋር ከተፈፀመ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፀነሰን ጽንስ ማስወረድ እንደቅጣት ማቅለያ ተደንግጎ ነበር። እነዚህ ሁለት ምክንያቶች በረቂቁ ውስጥ ፅንስን ለማስወረድ እንደተፈቀዱ ምክንያቶች ሆነው በረቂቁ አንቀጽ 534 ሀ ውስጥ እንዲካተቱ ሆኗል። ይህም የሆነበት ምክንያት በወቅቱ ይህ ጥያቄ ከህብረተሰቡ በመቅረቡ ነው።


ethcriminalawnetwork.com

## 14. በሰው አካልና በሰውጤና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ 538

በወ/መ/ህ/ ቁ.538 አስቦ ስለተደረገ ከባድና የአካል ጉዳት ቅጣቱ ከፍ ብሎ በረቂቁ ውስጥ ተካትቷል።

### አንቀጸ 543

በወ/መ/ሕግ ቁጥር 543 ላይ በቸልተኝነት በሰው አካል ላይ ስለሚፈፀም ጉዳት የተደነገገው በትራንስፖርት አሽከርካሪዎች፣ በሐኪሞች ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት ለሌሎች ሰዎች ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ እያለባቸው ይህንን ቸል በማለት በሰው ጤንነት ላይ ወይም ሰውነት ላይ ጉዳት ሲያደርሱ ከፍተኛ ቅጣት እንደሚወሰንባቸው በሚያስተምርና በሚያስጠነቅቅ መልኩ ተሻሽሎ ተረቅቋል።

### አንቀጽ 544 ሀ

ይህ ድንጋጌ የሴት ልጆችን መግረዝ በጎጂ ባህልነቱ በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ ተወሰዶበት በሴቶች ጉዳይ ከሚኒሱት ጥያቄዎች አንዱ ሆኖ በመገኘቱ ይህንን ተግባር መፈፀም በወንጀል እንደሚያስጠይቅ በረቂቁ ውስጥ ተደንግጓል።

### አንቀጽ 557-ሀ

በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጠለፋን በሴት ላይ እና አካለ መጠን ባላደረሱ ልጆች ላይ ሲፈፀም እንደሚያስቀጣ የደነገገ ነበር፣ይህ ወንጀል በማንም ሰው ላይ ሊፈፀም እንደሚቻል ግንዛቤ በመውሰድ ይህ አዲስ አንቀጽ በረቂቁ ውስጥ ሌሎቹንም ሰዎች በሚሸፍን መልኩ እንዲካተት ይሆኗል።

### አንቀጽ 564

በሥራ ላይ ያለው የወ/መ/ሕግ ቁ. 564 በፖለቲካ ምክንያት ሰውን ጠልፈው ለሌላ ፖለቲካ ድርጅት የሚሰጡትን ለመቅጣት የደነገገው አሳልፎ መስጠቱን ወደሌላ ሐገር ከማስወጣት ጋር በተያያዘ መልኩ ነው። ይህ አቀራረጽ በሐገር ውስጥ በተለያየ ሁኔታ በፖለቲካ ምክንያት ሌላውን ሰው ጠልፎ መያዝን ስለማያካትት ይህንን በአካተተ መልኩ ተሻሽሎ እንዲቀረጽ ሆኗል።

### አንቀጽ ቁጥር 587

ይህ ድንጋጌ የሚያወሳው ክስ በተበዳይ ሰው አቤቱታ አቅራቢነት መሆኑን ሲሆን ይህ አባባል ከቁጥር 580-586 ባሉት ድንጋጌዎች ክስ


ethcriminalawnetwork.com

የሚቀርበው በተበዳዩ መሆኑ ታክሎ የተረቀቀ ስለሆነ፣ ቁጥር 587 እንዲሰረዝ ተደርጓል።

## አንቀጽ 589

የወ/መ/ሕግ ቁ፲ 589 የመነሻ ቅጣቱ አንሶ በመገኘቱ ከፍ እንዲል ሆኖ ተሻሽሏል። እንዲሁም የዚሁ ሰለባ ሊሆኑ የሚችሉ በአካል ወይም በመንፈስ ጉዳት ሥር ያሉ ሰዎችንም የሕግ ጥበቃ ግልጽ በሆነ መልኩ በተለየ ንዑስ ቁጥር እንዲካተት ተደርጓል። ከዚህ ወንጀል መፈፀም ጋር ተያይዘው የሚከተሉ ጉዳቶች ማለትም፣ የአካል ጉዳት፣ በግብረ ሥጋ በሚተላለፍ በሽታ መያዝ፣ ወይም የሕይወት ማለፍ ቢከተል፣ ለእነዚሁ ወንጀሎች የተደነገጉት በተደራቢነት በአጥፊው ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ሆኖ ተሻሽሎ ተረቅቋል።

## አንቀጽ 595

በሥራ ላይ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 594 ላይ የተደነገገው አሥራ አምስት ዓመት ባልሞላት ሕፃን ላይ የሚፈፀምን የክብረንጽህና በደል ሲሆን ቁጥር 595 ደግሞ የሚደነግገው የክብረንጽህና በደሉ ከ15-18 ዓመት ባለ ሕፃን ላይ ሲፈፀም ነው። በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥትም ሆነ በሕፃናት ኮንቬንሽን ዕድሜው 18 ያልሞላ ሁሉ አካለ መጠን እንዳልደረሰ ስለሚቆጠር በቁጥር 545 ላይ ያለው የወንጀል ድርጊት በቁጥር 594 ላይ በተደነገገው ድንጋጌ ላይ አካለ መጠን ባለዳረሱ ልጆች ላይ ስለሚፈጸም የግብረ ሥጋ በደል በሚል ተጠቃልሎ ስለተቀረጸ ቁ.595 ተሠርዟል።

## 15. በመልካም ጠባይ / ሞራል/ ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች

## አንቀጽ 610፣612፣613፣

እነዚህ ቁጥሮች የሚደነግጉት ጸያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ለሕዝብ ስለመግለጽ/ ማሳየት ሲሆን በሥራ ላይ በአለው ሕግ ለእነዚህ ወንጀሎች የተደነገገው የቅጣት መጠን አነስተኛ ነበር፣ በተለይም የወጣቶችን ደህንነት ሥነምግባር ከመጠበቅ አንጻር በዚህ ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ከህብረተሰቡ በየወቅቱ አስተያየት የተሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ፣ ድንጋጌዎቹ ወንጀልን፣ ነጂ ልማድን የሚያራምዱ የቪዲዮ ፊልሞችን ስርጭት ጭምር ለመከላከል በሚረዳ መልኩ፣ ቅጣቱ ከፍ ብሎ ተረቅቋል።


ethcriminalawnetwork.com

## 16. በጋብቻ ሥርዓት ላይ ስለሚፈጽሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ 615፣

ይህ ድንጋጌ በሕግ የተደነገጉ ሁኔታዎችን ያላሟላ ጋብቻ የሚያስፈጽሙትን ሰዎች ብቻ በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርግ ስለነበር። ጋብቻ ፈጻሚዎችን፣ ምስክሮችንም እንደአግባብነቱ ተጠያቂ በሚያደርግ መልኩ ተሻሽሎ ተረቅቋል

## 17. በንብረት ላይ ስለሚፈፀም ወንጀል

### አንቀጽ 633፣

ይህ ድንጋጌ ከሬሳ ጋር የተቀበሩ ዕቃዎችን የሰረቀ ብቻ ተጠያቂ የሚሆንበትን ሁኔታ ብቻ የሚመለከት ነበር፣ ነገር ግን በተግባር ከአስከሬኑ ላይ እንደጥርስ ወርቅ የመሳሰሉት የሚሰረቁበት ሁኔታ ምናልባትም ከአስከሬኑ ክፍል የሚሰረቅ ቢኖር ይህንንም እንዲሸፍን ተደርጎ ተሻሽሎ ተረቅቋል።

### አንቀጽ 635፣

በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ቀድሞ ያልነበረ በአብያተ ሃይማኖት አገልጋዮች የቅርስ ስርቆት በሚፈፀምበት ጊዜ ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጎ፣ በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የቅርስ ስርቆት ለመከላከል በሕጉ የተሰጠውን ትኩረት አጉልቶ ለማሳየት በሚረዳ መልኩ ተሻሽሎ ተረቅቋል።

### አንቀጽ 641፣642

ይህ ድንጋጌ እምነት ማጉደልን የሚሸፍን ሲሆን፣ በአዋጅ ቁ.214/74 አንቀጽ 13 ሆኖ፣ የሕዝባዊ ድርጅቶችን ንብረት በመሸፈንና፣ የማኅበራትን ንብረት ያንቀሳቅሱትን ጭምር በመሸፈን፣ ቅጣቱ ከፍ ተደርጎ ተሻሽሎ ነበር፣ በአዲሱ ረቂቅ የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 13 ድንጋጌ ያዘላቸውን ጉዳዮች በያዘ መልኩ አንቀጾቹ የበለጠ ግልጽነት እንዲኖራቸው ሆኖ ተሻሽሎ ተረቅቋል።


ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 642.ሀ

ይህ ድንጋጌ በሥራ ላይ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ ያልነበረ ሲሆን በልዩ ወ/መ/ሀ/ቁ. 214/74 አን.14 ላይ በመንግሥት እና በሕዝብ ንብረት ያለአግባብ ስለመገልገልና ማባከንን የሚሸፍን ሆኖ ተደንግጎ ነበር፣ ይህ ድንጋጌ አስፈላጊ በመሆኑ ወደረቂቁ አንቀጽ 642 ሀ በሚል ተሻሽሎ እንዲገባ ተደርጓል።

## አንቀጽ 645 (2)

በሥራ ላይ ባለው ሕግ የተደበቀ ወይም የተቀበረ ገንዘብን አግኝቶ አለማሳታወቅን ፣ እንዲሁም ከተገኘው ገንዘብ ለቦታው የግል ባለቤት የሚሰጠውን ክፍያ አለመክፈልን በሸፈነ መልኩ ነበር፤ በመሬት ውስጥ ተደብቆ ወይም ተቀብሮ የሚገኘው ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች እንደወርቅ የመሳሰሉ ንብረቶችም ስለሚሆኑና፣ መሬትም የመንግሥት በመሆኑ፣ እነዚህን ሁኔታዎች በሸፈነ መልኩ ተሻሽሎ ተረቅቋል።

## አንቀጽ 646

ይህ ድንጋጌ በመሠረቱ የወንጀል ድንጋጌ ይዘት የሌለው እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተሸፈኑትን ለማመላከት ብቻ የገባ በመሆኑ ያለዚህ ድንጋጌ ሌሎቹ ድንጋጌዎች በራሳቸው ተፈጻሚ ስለሚሆኑ፣ ይህ ቁጥር በረቂቁ ውስጥ እንዲሰረዝ ሆኗል።

## 18. ደንብ መተላለፍ

## አንቀጽ 691

ይህ ድንጋጌ ስለደንብ መተላለፍ ትርጉም የሚሰጥ ሲሆን በሥራ ላይ ያለው ድንጋጌ የተቀረጸው በ1948 በተሻሻለው ሕግ መንግሥት የሕግ፣ የደንብ/ ትዕዛዝ ሕግ ክፍል ማስታወቂያ አወጣጥ ሥርዓት መሠረት የአስፈጻሚው አካል መሥሪያ ቤቶች እነዚህን የሚያውጁበትን ሁኔታ በሸፈነ መልኩ ነበር፣ ሆኖም በኢፌዴሪ ሕገ ለ መንግሥት ደንብ የማውጣት ሥልጣን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመሆኑ ይህንኑ በአንጻባረቀ መልኩ ረቂቁ ተሻሽሏል።



ethcriminalawnetwork.com

## አንቀጽ 725፣727

በሥራ ላይ ያለው ሕግ ስለጥፋት መደራረብ እና ተደጋግሞ መሠራት የሚደነግገው ግልጽነት የጎደለውና አሻሚ ስለነበር፣ ለአፈጻጸም ግልጽ በሆነ መልኩ ተሻሽሎ ተረቅቋል።

## አንቀጽ 732

በሥራ ላይ ባለው ሕግ በደንብ መተላለፍ የተቀጣ ሰው እንደ መደበኛ ወንጀል ተቀጪ የመሰየም ሥርዓት ውስጥ የሚገባበት ሁኔታን የሸፈነ ነበር፤ ይህንን ሥርዓት በደንብ መተላለፍ ላይ ተፈጻሚ ማድረግ፣ ቀላል የሆነን ደንብ መተላለፍ የፈፀመውንና መደበኛ ወንጀል የፈፀመውን ሰው በአንድ መልክ መፈረጅ ስለሚሆንና በአፈጻጸም ረገድ በፍርድ ቤቶች ላይ አላስፈላጊ ከፍተኛ ጫና መፍጠር ስለሚሆን፣ ቅጣቱ ከተፈጸመ አንድ ዓመት ካለፈው በሕጉ አማካይነት ተቀጪው እንደተሰየመ እንዲቆጠር በሚል ተሻሽሎ ተረቅቋል።

## አንቀጽ 776(ለ)

ይህ በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 776(ለ) የሚደነግገው ስለላንሱር ወይም ቅድመ ምርመራ በመሆኑና ይህም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት ቀሪ የሆነ በመሆኑ፣ በዚህ ምክንያት ይህ ቁጥር በአዲሱ ረቂቅ ላይ እንዳተሰረዘ ተመልክቷል።

## አንቀጽ 802 (ሀ)

ይህ ድንጋጌ በሌላ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ፊደል ለ ላይ ያለው በረቂቁ አንቀጽ 802 ሆኖ ተረቅቋል።



ethcriminalawnetwork.com